የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፯
አዲስ አበባ ጥቅምት ፴ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 67
ADDIS ABABA 9th November 2009

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፷፱/፪ሺ፩
የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትና የማህበረሰብ መብቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ............ገጽ ፭ሺ፸፩

CONTENTS

Regulation No. 169/2009
Access to Genetic Resources and Community Knowledge, and Community Rights Council of Ministers Regulation ............Page 5071

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፱/፪ሺ፩

## የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትና የማህበረሰብ መብቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትና የማህበረሰብ መብቶችን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፹፪/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፴፯ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ ‹‹የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ መብቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፱/፪ሺ፩›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ ‹‹የአርክቦት ውል›› ማለት የጀነቲክ ሀብት እና/ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ለማርከብና ከዚያም የሚገኘውን ጥቅም ለመጋ ራት በአዋጁ አንቀጽ ፲፬ (፪) መሠረት የሚፈረም ስምምነት ነው፤

Council of Ministers Regulation No. 169 /2009

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR ACCESS TO GENETIC RESOURCES AND COMMUNITY KNOWLEDGE, AND COMMUNITY RIGHTS

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 37 of the Access to Genetic Resources and Community Knowledge, and Community Rights Proclamation No. 482/2006.

### PART ONE
### General Provisions

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as the "Access to Genetic Resources and Community Knowledge, and Community Rights Council of Ministers Regulation No. 169/2009".

2 *Definition*

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. "access agreement" means an agreement, signed in accordance with Article 14(2) of the Proclamation, on the access to, and sharing the benefits arising from the utilization of, genetic resources and/or community knowledge;

፪/ ‹‹የአርክቦት አመልካች›› ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፲፬ (፩) መሠረት የአርክቦት ማመልከቻ ለኢንስቲትዩቱ ያቀረበ ሰው ነው፤

፫/ ‹‹የአርክቦት ማመልከቻ›› ማለት የጀነቲክ ሀብት እና/ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ለማርከብ በአዋጁ አንቀጽ ፲፬(፩) መሠረት ለኢንስቲትዩቱ በጽሑፍ የቀረበ ጥያቄ ነው፤

፬/ ‹‹የአርክቦት ገንዘብ›› ማለት በአርክቦት ውል መሠረት የጀነቲክ ሀብት እና/ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ጥቅም ላይ በመዋሉ ከተገኘው ገቢ በጥቅም ተጋሪነት የሚገኝ ገንዘብ ነው፤

፭/ ‹‹ሥልጣን ያለው አካል›› ማለት በአርክቦት አመልካቹ ሀገር ውስጥ የአርክቦት ውልን ለማስፈጸም ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካል ነው፤

፮/ ‹‹የማህበረሰብ እሺታ›› ማለት የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትን ለመፍቀድ የአካባቢ ማህበረሰቦች በአዋጁ አንቀጽ ፯ (፩) (ሀ) መሠረት የሚሰጡት አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

፯/ ‹‹ኢንስቲትዩት›› ማለት በአዋጅ ቁጥር ፩፻፳/፲፱፻፺(እንደተሻሻለ) የተቋቋመው የብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ነው፤

፰/ ‹‹ዓለም አቀፍ ስምምነት›› ማለት በተባበሩት መንግሥታት የምግብና እርሻ ድርጅት ሰላሳ አንደኛ ጉባኤ እ.ኤ.አ. በኖቬምበር ፫ ቀን ፪ሺ፩ የፀደቀው እና በአዋጅ ቁጥር ፫፻፴/፲፱፻፺፭ ኢትዮጵያ ያፀደቀችው የምግብና ግብርና ዕፀዋት ጀኒቲክ ሀብት ዓለም አቀፍ ስምምነት ነው፤

፱/ ‹‹የባለብዙ ወገን አርክቦት ሥርዓት›› ማለት በዓለም አቀፍ ስምምነቱ አንቀጽ ፲ መሠረት የምግብና ግብርና ዕፀዋት ጀነቲክ ሀብቶችን አርክቦት እና ከዚያም የሚገኘውን ጥቅም ፍትሐዊና ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ መጋራትን ለማቀላጠፍ የተመሠረተው ሥርዓት ነው፤

፲/ ‹‹አዋጅ›› ማለት የጀነቲከ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ መብቶች አዋጅ ቁጥር ፬፻፹፪/፲፱፻፺፰ ነው፤

፲፩/ ‹‹አግባብነት ያለው የክልል አካል›› ማለት የጀነቲክ ሀብት እና/ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን እንዲያስተዳድር ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤት ነው፤

፲፪/ ‹‹የጀነቲክ ቁስ ማስተላለፊያ መደበኛ ውል›› ማለት በዓለም አቀፍ ስምምነቱ አንቀጽ ፲፪ መሠረት የፀደቀው የምግብና ግብርና ዕፅዋት ጀነቲክ ሀብት ቁስ ማስተላለፊያ ስምምነት ነው፤

2. "access applicant" means a person who has lodged an access application to the Institute pursuant to Article 14 (1) of the Proclamation;

3. "access application," means a written request presented to the Institute, in accordance with Article !4(1) of the Proclamation, to access genetic resources and /or community knowledge;

4. "access money" means the money obtained from access agreements by way of sharing the benefits arising from the utilization of genetic resources and /or community knowledge;

5. "competent authority" means a government organ of the country of the access applicant that is empowered to ensure the implementation of access agreements;

6. "community consent" means the prior informed consent given by local communities, in accordance with Article 7(1) (a) of the Proclamation, to allow access to their community knowledge;

7. "Institute" means the Institute of Biodiversity Conservation established by Proclamation No. 120/1998 (as amended);

8. "International Treaty" means the International Treaty on Plant Genetic Resources for Food and Agriculture which was adopted on the 3rd day of November 2001 at the Thirty-First Conference of the Food and Agriculture Organization of the United Nations, and which Ethiopia ratified by Proclamation No. 330/2003,

9. "multilateral system of access" means the system established in accordance with Article 10 of the International Treaty in order to facilitate the access to, and a fair and equitable sharing of the benefits arising from the utilization of , plant genetic resources for food and agriculture;

10. "Proclamation" means the Access to Genetic Resources and Community Knowledge, and Community Rights Proclamation No. 482/2006;

11. "relevant regional body" means an organ of a regional state having the power and responsibility to administer genetic resources and/or community knowledge in the region;

12. "standard material transfer agreement" means the material transfer agreement adopted under Article 12 of the International Treaty;

፲፫/ ‹‹አርክቦት››፣ ‹‹የጀኔቲክ ሀብት››፣ ‹‹የማህበረሰብ ዕውቀት››፣ ‹‹የአካባቢ ማህበረሰብ››፣ ‹‹ሰው››፣ ‹‹አግባብነት ያለው ተቋም›› እና ‹‹መንግሥት›› የሚሉት ቃላት በአዋጁ የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፤

፲፬/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የአርክቦት ሥነ-ሥርዓት
### ንዑስ ክፍል አንድ
### ለንግድ ዓላማ የሆነ አርክቦት ስነ-ሥርዓት

**፫. የአርክቦት ማመልከቻ አቀራረብ**

የጀኔቲክ ሀብት እና/ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን ለማርከብ በአዋጁ አንቀጽ ፲፬(፩) መሠረት የሚቀርበውን የአርክቦት ማመልከቻ በዚህ ደንብ አባሪ-፩ ላይ በተገለጸው መሠረት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

**፬. የአርክቦት ማመልከቻን ስለመቀበል**

ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ማመልከቻ ሲቀርብለት፡-

፩/ የአርክቦት ማመልከቻው በዚህ ደንብ አባሪ -፩ ውስጥ የተገለፁትን መረጃዎች አሟልቶ የቀረበ መሆኑን ካረጋገጠ ማመልከቻውን በመቀበል በአርክቦት መዝገብ ላይ ይመዘግባል፤ ወይም

፪/ የአርክቦት ማመልከቻው በዚህ ደንብ አባሪ-፩ ላይ የተገለፁትን መረጃዎች አሟልቶ የቀረበ አለመሆኑን ካረጋገጠ የሚጎድለውን መረጃ በመግለጽ ተሟልቶ እንዲቀርብ ለአማልካቹ ይመልስለታል፡፡

**፭. የአርክቦት ማመልከቻን ስለመመርመር**

፩/ ኢንስቲትዩቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሠረት ተቀብሎ የመዘገበውን የአርክቦት ማመልከቻ፣ ከአዋጁ ድንጋጌ እና ቀደም ሲል ከተፈረሙ የአርክቦት ውሎች አንፃር በመመርመር የተጠየቀው አርክቦት ሊፈቀድ የሚችል ወይም መከልከል ያለበት መሆኑን ይወስናል፡፡

፪/ ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ማመልከቻውን ከመረመረ በኋላ፡-

ሀ) የተጠየቀውን አርክቦት ለመፍቀድ የሚከለክል በቂ ምክንያት መኖሩን ካረጋገጠ፣ አርክቦቱን በመከልከል የከለከለበትን ምክንያት በመግለጽ ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቃል፤ ወይም

ለ) የተጠየቀውን አርክቦት መፍቀድ የሚከለክል ምክንያት አለመኖሩን ካረጋገጠ ማመልከቻው ለሕዝብ እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡

13. the terms "access", "genetic resource", "community knowledge" "local community", "person", "relevant institution" and "state" shall have the meaning given to them in the Proclamation;

14. any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO
## PROCEDURE OF ACCESS
### SECTION ONE
### PROCEDURE FOR COMMERCIAL ACCESS

3. *Submission of Access Application*

The access application to be submitted pursuant to Article 14 (1) of the Proclamation to access genetic resources and/or community knowledge shall be presented in accordance with the form specified in Annex-I of this Regulation.

4. *Admission of Access Application*

Upon submission of an access application, the Institute shall:

1. admit the access application and register it in the access register, if it ascertains that the access application contains all the information required in Annex-I of this Regulation; or

2. return the access application to the applicant to be completed, stating the information missing, if it ascertains that the access application does not contain all the information required in Annex-I of this Regulation.

5. *Examination of Access Application*

1. The Institute shall, based on the provisions of the Proclamation and access agreements concluded hitherto, examine the access application admitted under Article 4 of this Regulation and determine whether it may be granted or should be denied.

2. Having examined the access application, the Institute shall:

(a) if it ascertains that there is sufficient ground to deny the proposed access, deny the proposed access and communicate the same to the applicant in writing stating the reasons for the denial; or

(b) if it ascertains that there is no ground sufficient to deny the intended access, give public notice of the access application.

፮. የአርክቦት ማመልከቻን ለሕዝብ ስለማገለጽ

፩/ ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ማመልከቻውን በአመልካቹ ወጪ ሰፊ ስርጭት ባለው ብሔራዊ ጋዜጣ እና እንደ ሁኔታው አርክቦቱ ሊፈፀም በታቀደበት አካባቢ በሚታተም የአካባቢ ጋዜጣ ላይ ታትሞ ለሕዝብ እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው የህዝብ ማስታወቂያ፦

ሀ) የአመልካቹን ማንነትና ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮችን፣

ለ) ማርከብ የተፈለገውን የጀነቲክ ሀብት እና/ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት መግለጫ፣ እና

ሐ) የጀነቲክ ሀብቱ እና/ወይም የማህበረሰብ ዕውቀቱ ሊውል የታሰበበትን አገልግሎት የሚገልጹ ዝርዝሮችን፣ መያዝ አለበት፡፡

፫/ ማናቸውም ሰው የሕዝብ ማስታወቂያው ለህዝብ ከተገለፀበት ዕለት አንስቶ በ፴ ቀናት ውስጥ በአርክቦት ማመልከቻው ላይ ተቃውሞ ለማቅረብ ወይም አስተያየት ለመስጠት ይችላል፡፡

፬/ ኢንስቲትዩቱ እንደ አስፈላጊነቱ አግባብነት ያላቸው ተቋማት በአርክቦት ማመልከቻው ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ለማድረግ ይችላል፡፡

፯. የአርክቦት መረጃ ለሕዝብ ግልጽ ስለማድረግ

የአርክቦት ማመልከቻ በማቅረብ ወይም አርክቦትን በመቆጣጠር ሂደት ለኢንስቲትዩቱ የሚቀርብ የአርክቦት መረጃ ለሕዝብ ግልጽ ይደረጋል፣ መረጃውን መመልከት የፈለገም ማንኛውም ሰው ሊመለከተው ይችላል፡፡

፰. በሚስጥር የሚያዝ መረጃ

፩/ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ድንጋጌ ቢኖርም፣ አሳማኝ ምክንያት በቀረበ ጊዜ ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ማመልከቻ በሚቀርብበት ወይም የአርክቦት ቁጥጥር በሚደረግበት ሂደት ለኢንስቲትዩቱ የሚቀርብ፣ በይፋ ያልተገለፀና በሦስተኛ ወገኖች ቅን ላልሆነ የንግድ ዓላማ ሊውል የሚችል የአርክቦት መረጃ ከ፲ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በሚስጥር እንዲያዝ ለመፍቀድ ይችላል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የአርክቦት አመልካቹን ማንነት፣ ለማርከብ የተፈለገውን የጀነቲክ ሀብት ዓይነት፣ የጀነቲክ ሀብቱ የሚገኝበትን አካባቢ፣ የጀነቲክ ሀብቱን የሚያቀርበው ሰው ማንነት ወይም የጀነቲክ ሀብቱ በሚሰበሰብበት ወቅት አብሮ የሚገኘውንና አርክቦቱን የሚቆጣጠረውን ተቋም ማንነት የሚመለከት መረጃ በሚስጥር እንዲያዝ አይፈቀድም፡፡

6. *Publication of Access Application*

1. Public notice of the access application shall be given, at the expense of the access applicant, in a national newspaper having wider distribution and, as appropriate, in the local newspaper of the locality where the access is intended to take place.

2. The public notice referred to in sub-article (1) of this Article shall contain the following particulars:

   (a) the identity and other necessary particulars of the applicant;

   (b) the description of the proposed genetic resource and/or the community knowledge; and

   (c) the proposed use of the genetic resource and/or the community knowledge.

3. Any person may lodge objection against, or give comment on, the access application within 30 days from the date of its publication.

4. The Institute may, as appropriate, also ask for the opinion of relevant institutions on the access application.

7. *Publicity of Access Information*

Any information communicated to the Institute in the course of access application or in the course of monitoring access shall be public and may be consulted by any interested person.

8. *Confidential Information*

1. Notwithstanding the provisions of Article 7 of this Regulation, the Institute may, upon acceptable justification, grant confidential treatment, for a period of not more than 10 years, to the information which shall be communicated to it in the course of access application or monitoring access and which has not been divulged and could be used for disloyal commercial purposes by third parties.

2. Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, confidentiality may not be granted to information on the identification of the applicant, the genetic resource to be accessed, the locality where the genetic resource is found, the supplier of the genetic resource or the relevant institution accompanying and monitoring the access.

፫/ የአርክቦት መረጃ በሚስጥር እንዲያዝለት የሚፈልግ የአርክቦት አመልካች፣ መረጃው በሚስጥር እንዲያዝ የሚያስፈልግበትን ምክንያትና በሚስጥር እንዲያዝ የተፈለገውን መረጃ በመግለጽ ጥያቄውን በጽሑፍ ለኢንስቲትዩቱ ማቅረብ አለበት፡፡

፬/ ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት መረጃ በሚስጥር እንዲያዝ ሲፈቅድ፣ በሚስጥር የሚያዘውን መረጃና በሚስጥር የሚቆይበትን ጊዜ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

፭/ ኢንስቲትዩቱ በሚስጥር እንዲያዝ የፈቀደውን መረጃ በተለየ ፋይል በማድረግ በሚስጥር ይይዛል፡፡

## ፱. በሚስጥር የተያዘ መረጃን ስለመግለጽ

፩/ በሚስጥር እንዲያዝ የተፈቀደ መረጃ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣ በሚስጥር እንዲያዝ የተፈቀደበት ጊዜ ሲያበቃ ወይም በተዋዋይ ወገኖች የጋራ ስምምነት መሠረት ካልሆነ በስተቀር ለሦስተኛ ወገን አይገለጽም፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም፣ ኢንስቲትዩቱ በሚስጥር እንዲያዝ የተፈቀደ መረጃን ሠራተኞቹ ወይም አማካሪዎቹ እንዲገመግሙት ሊገልጽላቸው ይችላል፤ ሆኖም ይህ በሚፈፀምበት ወቅት ኢንስቲትዩቱ መረጃው በሚስጥር የተያዘ መሆኑን ሠራተኞቹንና አማካሪዎቹን ማስገንዘብ አለበት፡፡

## ፲. የአርክቦት ውሳኔ አሰጣጥ

፩/ በአርክቦት ማመልከቻው ላይ ተቃውሞ ለማቅረብ ወይም አስተያየት ለመስጠት የተቀመጠው የጊዜ ገደብ እንዳበቃ፣ ኢንስቲትዩቱ የቀረቡለትን ተቃውሞዎችና አስተያየቶች በመመርመር፡-

ሀ) የአርክቦት ማመልከቻው ሊከለከል የሚችልበት ምክንያት መኖሩን ካረጋገጠ፣ የአርክቦት ማመልከቻውን ውድቅ በማድረግ ይህንኑ ለአመልካቹ ያሳውቃል ፤ ወይም

ለ) የአርክቦት ማመልከቻውን የሚያስከለክል ምክንያት አለመኖሩን ካረጋገጠ፣ አርክቦቱ ሊፈቀድ እንደሚችል በመወሰን የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ድርድር እንዲያደረግ ለአርክቦት አመልካቹ ያሳውቃል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) መሠረት ሊፈቀድ እንደሚችል የተወሰነ የአርክቦት ማመልከቻ የማህበረሰብ ዕውቀት ማርከብን የሚጨምር በሆነ ጊዜ፣ ኢንስቲትዩቱ በዚህ ደንብ ክፍል ሦስት በተገለጸው መሠረት የማህበረሰብ እሺታ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡

3. An access applicant who wishes a confidential treatment of access information shall present to the Institute a request in writing justifying the request for confidentiality and specifying the information to be confidential.

4. Where the Institute grants confidentiality, it shall specify the information to be confidential and the term of confidentiality.

5. The information to which confidential treatment has been granted shall be kept in a separate file under the custody of the Institute.

## 9. *Disclosure of Confidential Information*

1. Confidential information may not be communicated to third parties except upon court order, expiry of the period of confidentiality, or mutual agreement of the parties.

2. Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the Institute may disclose confidential information to its employees or consultants for purpose of evaluation; provided however, that it shall make its employees and consultants aware of the confidentiality of the information.

## 10. *Access Decision*

1. Upon the expiry of the time limit set for submission of objection and opinion, and having examined the public objections and opinions submitted, if any, the Institute shall:

(a) if it ascertains that there exists a sufficient ground to deny the proposed access, deny the access and inform the same in writing to the applicant indicating the reason for the denial; or

(b) if it ascertains that there exists no ground sufficient to deny access, it shall determine that the access may be granted and call upon the access applicant to negotiate an access and benefit agreement.

2. Where the access application which has been determined under sub-article (1) (b) of this Article that the access could be granted includes access to community knowledge, the Institute shall cause that community consent be given thereon in accordance with Part Three of this Regulation.

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ለንግድ ዓላማ ያልሆነ አርክቦት ሥነ-ሥርዓት

### ፲፩. የማመልከቻ አቀራረብ

በአዋጁ አንቀጽ ፲፭ መሠረት ለሚያከናውኑት የትምህርት ወይም የምርምር ተግባራት ለማዋል የጀነቲክ ሀብት እና/ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ማርከብ የሚፈልጉ የኢትዮጵያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና የምርምር ተቋማት እንዲሁም ተቀማጭነታቸው በኢትዮጵያ የሆነ የበይነ-መንግሥታት ተቋማት ለኢንስቲትዩቱ የሚያቀርቡት የአርክቦት ማመልከቻ በዚህ ደንብ አባሪ-፪ መሠረት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

### ፲፪. የፈቃድ አሰጣጥ

ኢንስቲትዩቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ መሠረት በኢትዮጵያ የትምህርት ወይም የምርምር ተቋም ወይም ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ በሆነ የበይነ-መንግሥታት ተቋም የአርክቦት ማመ ልከቻ ሲቀርብለት፤ አመልካቹ አርክቦቱን ሲያካሄድ የሚኖሩበትን ግዴታዎች በመወሰንና ለዚህም የአርክቦት ውል በማስፈረም የአርክቦት ፈቃድ ይሰጣል፡፡

### ፲፫. የጀነቲክ ሀብትን ከሀገር ስለማስወጣት

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ መሠረት የአርክቦት ፈቃድ የሚሰጣቸው የኢትዮጵያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና የምርምር ተቋማት እንዲሁም ተቀማጭነታቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የበይነ-መንግሥታት ተቋማት የጀነቲክ ሀብትን ወደ ውጭ እንዲልኩ ፈቃድ ካልተሰጣቸው በስተቀር የአረከቡትን የጀነቲክ ሀብት ከኢትዮጵያ ማስወጣት አይችሉም፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም፣ የኢትዮጵያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ወይም የምርምር ተቋም ወይም ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ የሆነ የበይነ-መንግሥታት ተቋም ምርምሩን ኢትዮጵያ ውስጥ ለማካሄድ የማይችል መሆኑን ኢንስቲትዩቱ ካረጋገጠ፣ የጀነቲክ ሀብትን ወደውጪ መላክ የሚችል መሆኑን በሚሰጠው የአርክቦት ፈቃድ ውስጥ ማመልከት ይችላል፡፡

፫/ ኢንስቲትዩቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የጀነቲክ ሀብትን ከኢትዮጵያ ለማስወጣት ፈቃድ ሲሰጥ፣ ሀገሪቱ በጀነቲክ ሀብቱ ላይ ያላትን መብት ሊያስጠብቅ የሚችልና የጀነቲክ ሀብቱ የሚወሰድበትን የውጭ ሀገር ተቋም ያካተተ የአርክቦት ውል ማስፈረምና የስምምነቱን አፈጻጸም መከታተል ይኖርበታል፡፡

## SECTION TWO

## PROCEDURE FOR NON-COMMERCIAL ACCESS

### 11. *Submission of Access Application*

The access application which Ethiopian higher learning and research institutions as well as inter-governmental institutions based in Ethiopia shall present to access genetic resources and/or community knowledge for purpose of their institutional activities in accordance with Article 15 of the Proclamation shall be presented in accordance with Annex-II of this Regulation.

### 12. *Granting of Permit*

Upon receipt of access application by national higher learning or research institution or an inter-governmental institution based in Ethiopia in accordance with Article 11 of this Regulation, the Institute shall, having determined the obligation the applicant shall have while having access and upon signing of access agreement to this effect, grant access to the applicant.

### 13. *Exporting of Genetic Resource*

1. Ethiopian higher learning and research institutions as well as inter-governmental institutions based in Ethiopia who are granted access permit in accordance with Article 12 of this Regulation, shall not export genetic resources out of Ethiopia unless they are given explicit permit to this effect.

2. Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, where the Institute ascertains that Ethiopian higher learning or research institution or an inter-governmental institution based in Ethiopia, can not undertake the research in Ethiopia, it may state in the access permit that it can export genetic resources out of Ethiopia.

3. Where the Institute grants permit to export genetic resources out of Ethiopia in accordance with sub-article (2) of this Article, it shall cause that an access agreement be concluded that enable protect the interests of the country over the genetic resource in question and that shall also bind the foreign institution where the research is intended to take place, and follow up and monitor the observance of such agreement.

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## የባለብዙ ወገን አርክቦት ሥነ ሥርዓት

**፲፬. የባለብዙ ወገን አርክቦት ቅድመ ሁኔታዎች**

በባለብዙ ወገን አርክቦት ሥርዓት መሠረት የጀነቲክ ሀብት አርክቦት የሚፈቀደው:-

፩/ የተጠየቀውን የጀነቲክ ሀብት ዓይነት በዓለም አቀፍ ስምምነቱ አባሪ-፩ ውስጥ ተጠቅሶ የሚገኝ ከሆነ እና የጀነቲክ ሀብቱ ለምግብና ግብርና ምርምር፣ ማዳቀልና ሥልጠና አገልግሎት ለመጠቀምና ለማንበር ብቻ የሚውል እና ይህም አገልግሎት ለኬሚካል፣ ለመድሀኒት እና/ወይም ለሌላ ለምግብ ወይም ለመኖ ያልሆነ ኢንዱስትሪያዊ አገልግሎት ማዋልን የማይጨምር ከሆነ፣

፪/ የአርክቦት አመልካቹ የዓለም አቀፍ ስምምነቱ ፈራሚ የሆነ ሀገር ዜጋ ወይም ነዋሪ ከሆነ፣ እና

፫/ የጀነቲክ ሀብቱ ለሕዝብ ጥቅም አገልግሎት እንዲውል በኢትዮጵያ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የዘቦታ ወይም የኢዘቦታ ጥበቃና አስተዳደር ስር የሚገኝ ከሆነ ወይም የጀነቲክ ሀብቱ ባለይዞታ የሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሰው የጀነቲክ ሀብቱ በባለብዙ ወገን አርክቦት ሥርዓቱ ውስጥ እንዲካተት የፈቀደ በሆነ ጊዜ ብቻ፣

ነው።

**፲፭. የአርክቦት ማመልከቻ**

በባለብዙ ወገን አርክቦት ሥርዓት መሠረት የጀነቲክ ሀብት ለማርከብ የሚፈልግ ሰው በዚህ ደንብ አባሪ-፫ በተገለጸው መሠረት የተዘጋጀ የአርክቦት ማመልከቻ ለኢንስቲትዩቱ ማቅረብ አለበት።

**፲፮. የባለብዙ ወገን አርክቦት ውሳኔ አሰጣጥ**

ኢንስቲትዩቱ የቀረበለትን የባለብዙ ወገን አርክቦት ማመልከቻ ከመረመረ በኋላ:-

፩/ የአርክቦት ማመልከቻው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ የተጠቀሱትን የባለብዙ ወገን አርክቦት ቅድመ ሁኔታዎች ያሟላ መሆኑን ካረጋገጠ፣ የባለብዙ ወገን አርክቦት ፈቃድ ለአመልካቹ ይሰጣል፤ ወይም

፪/ የአርክቦት ማመልከቻው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ የተጠቀሱትን የባለብዙ ወገን አርክቦት ሥርዓት ቅድመ ሁኔታዎች የማያሟላ መሆኑን ካረጋገጠ፣ አርክቦቱን በመከልከል ይህንኑ ለአመልካቹ ያሳውቃል።

**፲፯. የአርክቦት ክፍያ**

፩/ የባለብዙ ወገን አርክቦት የተፈቀደለት አመልካች የጀነቲክ ሀብቱን ለማቆየትና ለእርሱ ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ወጪ መሸፈን ይገባዋል። ይህም የጀነቲክ ሀብቱን ለመጠበቅ የወጣውን ወጪ፣ ናሙናው ሊሰጠው የሚችለው ተባዝቶ ወይም ተሰብስቦ ከሆነ ለማባዛት ወይም ለመሰብሰብ የሚያስፈልገውን ወጪ፣ እንዲሁም ናሙናው ከበሽታ ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ ለማሸግና በፖስታ ለመላክ የሚያስፈልጉ እና የመሳሰሉ ወጪዎችን ይጨምራል።

## SECTION THREE

## PROCEDURE FOR MULTILATERAL SYSTEM OF ACCESS

14. *Conditions of Multilateral System of Access*

Access to genetic resources in accordance with the multilateral system of access shall be granted only if:

1. the type of the genetic resource requested is listed in Annex-I of the International Treaty and the intended use of the genetic resource is solely for the purpose of utilization and conservation for research, breeding and training for food and agriculture, provided that such use does not include chemical, pharmaceutical and /or other non-food or feed industrial uses;
2. the access applicant is a citizen of a country that is party to the International Treaty; and
3. the requested genetic resource is under the ex situ or in situ management and control of the Ethiopian government organs or the possessor thereof has consented to conducting of the multilateral system of access.

15. *Access Application*

A person who wants to access genetic resources under the multilateral system of access shall present to the Institute an access application in the form stated in Annex-III of this Regulation.

16. *Decision on Multilateral Access*

Having examined the access application under the multilateral system, the Institute shall:

1. if the conditions of multilateral system of access stipulated under Article 14 of this Regulation are met, grant to the applicant access under the multilateral system of access; or
2. if the access application does not meet the conditions of multilateral system of access stipulated under Article 14 of this Regulation, deny the access and notify the same to the applicant.

17. *Access Fee*

1. An access applicant, who is granted access under the multilateral system of access, shall pay for the cost for maintaining and for providing him the genetic resource. Such costs shall include the cost for maintaining the sample, multiplication, collection, packaging, postage, phytosanitary certification and the like.

፪/ ኢንስቲትዩቱ የባለብዙ ወገን ጀነቲክ ሀብት አርክቦት ፈቃድ ሲሰጥ አመልካቹ መክፈል የሚገባውን የአርክቦት ክፍያ ይወስናል፡፡

፲፰. የተቀላጠፈ አርክቦት ስለመስጠት

ኢንስቲትዩቱ የባለብዙ ወገን የአርክቦት ፈቃድ ሲሰጥ፣ ሌላ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ ሳይጠይቅ የጀነቲክ ሀብት ቁስ ማስተላለፊያ መደበኛ ውል በማስፈረምና የአርክቦት ክፍያ በማስከፈል የጀነቲክ ሀብቱን ካለው የፓስፖርት መረጃና ሚስጥር ያልሆኑ ተያያዥ ገላጭ መረጃዎች ጭምር ለአመልካቹ ይሰጣል፡፡

፲፱. ክትትልና ቁጥጥር

ኢንስቲትዩቱ በባለብዙ ወገን አርክቦት ሥርዓት መሠረት የሰጠው የጀነቲክ ሀብት በተፈረመው የጀነቲክ ቁስ ማስተላለፊያ መደበኛ ውል መሠረት ጥቅም ላይ መዋሉን በመከታተልና በመቆጣጠር አግባብነት ባለው ህግ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

፳. ክስ ስለማቅረብ

የጀነቲክ ቁስ ማስተላለፊያ መደበኛ ውል አፈጻጸምን አስመልክቶ የሚነሳ ክርክር ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡

ክፍል ሦስት

የማህበረሰብ እሺታ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

፳፩. እሺታ የሚሰጠውን ማህበረሰብ ስለመለየት

፩/ የማህበረሰብ ዕውቀትን ለማርከብ ለሚቀርብ የአርክቦት ማመልከቻ እሺታ የሚሰጠው የዕውቀቱ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ ነው፡፡

፪/ የማህበረሰብ ዕውቀትን ለማርከብ ማመልከቻ ሲቀርብለት፣ ኢንስቲትዩቱ ቀደም ሲል ባካሄደው የጀነቲክ ሀብት እና/ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ስርጭት አሰሳ ላይ በመመስረትና አግባብነት ካላቸው የክልል አካላት ጋር በመመካከር የማህበረሰብ ዕውቀቱ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ እንዲለይና የማህበረሰብ እሺታ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡

፳፪. የማህበረሰብ እሺታ አሰጣጥ

የማህበረሰብ እሺታ የሚሰጠው ፤ የማህበረሰብ ዕውቀቱ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ የሚገኘው:-

፩/ በአንድ ወረዳ ውስጥ ብቻ ከሆነ፣ በወረዳው ምክር ቤት፣

፪/ በአንድ ክልል ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች ወይም ዞኖች ውስጥ ከሆነ፣ ከእነዚህ ወረዳዎች ወይም ዞኖች የተወከሉ የክልል ምክር ቤት አባላትን በማካተት በሚቋቋም የክልል ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴ፣ ወይም

2. Upon granting access under the multilateral system, the Institute shall determine the access fee to be paid.

18. *Provision of Facilitated Access*

Where the Institute grants access under the multilateral system of access, it shall provide the requested genetic resource together with the passport data and other non-confidential descriptive data to the applicant without any other requirement, upon signing of the standard material transfer agreement and payment of the access fee.

19. *Follow up and Monitoring*

The Institute shall follow up and monitor whether the utilization of the genetic resource provided is in compliance with the standard material transfer agreement and take the necessary measure in accordance with applicable laws.

20. *Claims*

Claims arising in relation to the implementation of the standard material transfer agreements may be presented to the Federal High Court.

PART THREE

COMMUNITY CONSENT PROCEDURE

21. *The Community Giving Consent*

1. The community which is the custodian of the community knowledge shall give consent to the access application thereto.
2. Upon receipt of an access application to access community knowledge, the Institute shall, based on the survey it has undertaken on the distribution of genetic resources and/or community knowledge and in consultation with the relevant regional bodies, cause that the community which is the custodian of the community knowledge be identified and community consent given thereon.

22. *Community Consent How Given*

Community consent shall be given:

1. where the community giving consent resides only in one Woreda, by the Wereda Council;
2. where the community giving consent resides in different Woredas or Zones of one region, by the provisional committee of the regional council consisting members represented from such Woredas or Zones;

፫/ በተለያዩ ክልሎች ውስጥ ከሆነ፣ ማህበረሰቡ ከሚገኝባቸው አካባቢዎች የተወከሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትን በማካተት በሚቋቋም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴ፣

አማካይነት ይሆናል፡፡

፳፫. <u>የአርክቦት ማመልከቻን ለእሺታ ስለማቅረብ</u>

ለማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት ማመልከቻው እሺታ የሚሰጠው ማህበረሰብ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፩(፪) መሠረት ተለይቶ እንደታወቀ ኢንስቲትዩቱ፦

፩/ የማህበረሰብ እሺታ የሚሰጠው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚቋቋም ጊዜያዊ ኮሚቴ ከሆነ፣ የአርክቦት ማመልከቻውን ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፤

፪/ የማህበረሰብ እሺታ የሚሰጠው በወረዳ ምክር ቤት ወይም በክልል ምክር ቤት በሚቋቋም ጊዜያዊ ኮሚቴ ከሆነ፣ የአርክቦት ማመልከቻውን ከውሳኔ ሀሳብ ጋር እሺታውን ለሚሰጠው የወረዳ ምክር ቤት ወይም የክልል ምክር ቤት እንዲያቀርብ አግባብነት ላለው የክልል አካል ያስተላልፋል፡፡

፳፬. <u>የእሺታ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት</u>

፩/ የወረዳ ምክር ቤቶች፣ የክልል ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴዎች እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴ ዎች የማህበረሰብ እሺታ የሚሰጡት የምክር ቤቶቻቸውን የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት በመከተል ይሆናል፡፡

፪/ የወረዳ ምክር ቤቶች፣ የክልል ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴዎች እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴ ዎች የሚሰጡት ውሳኔ ቅጂ ለኢንስቲትዩቱ ቀርቦ ከአርክቦት መዝገቡ ጋር ይያያዛል፡፡

፳፭. <u>ወጪን ስለመሸፈን</u>

የማህበረሰብ እሺታ ለማስጠት የሚያስፈልገውን ወጪ የአርክቦት አመልካቹ ይሸፍናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>የአርክቦት ገንዘብ አስተዳደርና አጠቃቀም</u>

፳፮. <u>የአርክቦት ገንዘብ አስተዳደር</u>

፩/ ከጀነቲክ ሀብት እና/ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት የሚገኘው ገንዘብ ሁሉ ጥቅም ላይ እስከሚውል ድረስ «የአርክቦት ፈንድ» በሚሰኝ ልዩ ሂሳብ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

3. where the community giving resides in an area which falls in different regions, by the provisional committee of the House of Peoples' Representatives consisting of members represented from such area where the community resides.

23. *Submission of Access Application for Community Consent*

Upon identification of the community which shall give community consent for the access application in accordance with Article 21(2) of this Regulation, the Institute shall:

1. where the community consent shall be given by the provisional committee of the House of Peoples' Representatives, submit to the House of Peoples' Representatives, the access application together with decision proposal thereon; or

2. where the community consent shall be given by the Wereda Council or the provisional committee of the Regional Council, submit the access application to the relevant regional body so that it shall submit to the Wereda Council or the Regional Council the access application together with decision proposal thereon.

24. Procedure of Giving Community Consent

1. The Wereda Council or the provisional committees of the Regional Council or the House of Peoples' Representatives shall give community consent in accordance with the procedure of their respected councils.

2. The copy of the community consent given by the Wereda Council or the provisional committee of the Regional Council or the House of Peoples' Representatives shall be sent to the Institute and filed with the access register.

25. *Cost*

The access applicant shall cover the cost required for obtaining community consent.

## <u>PART FOUR</u>
## <u>ADMINISTRATION AND UTILIZATION OF ACCESS MONEY</u>

26. *Administration of Access Money*

1. All the money obtained from access to genetic resources and/or community knowledge shall be deposited in a special account called "access fund"

፪/ ከእያንዳንዱ የአርክቦት ውል የሚገኝ ገንዘብ በተለየ የባንክ ሂሳብ ሆኖ በአርክቦት ፈንዱ ውስጥ ተለይቶ ይቀመጣል።

፫/ ኢንስቲትዩቱ የእያንዳንዱ የአርክቦት ውል ዘመን ሲያበቃ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከዚያም በፊት በማናቸውም ጊዜ የአርክቦት ገንዘቡ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፯ እና ፳፰ በተደነገገው መሠረት ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል።

## ፳፯. የአርክቦት ገንዘብን ለብዝሀ ህይወት ጥበቃ ስለማዋል

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፰(፩) መሰረት ለብዝሀ ህይወትና ለማህበረሰብ ዕውቀት ጥበቃ እንዲውል የተመደበው የአርክቦት ገንዘብ፣ ገንዘቡን ያስገኘውን የጀነቲክ ሀብት ለመጠበቅ፣ ወይም ገንዘቡን ያስገኘው የጀነቲክ ሀብት የመመናመን አደጋ ከሌለበት ሌሎች የጀነቲክ ሀብቶችን ለመጠበቅና በዘላቂነት ለመጠቀም እንዲሁም ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀቶችን ለመጠበቅ ለሚነደፉ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ይውላል።

፪/ የአርክቦት ገንዘቡ ጥቅም ላይ የሚውልባቸው የብዝሃ ሕይወት ጥበቃ ፕሮጀክቶች የሚመረጡት ኢንስቲትዩቱ አግባብነት ላላቸው የክልልና የፌዴራል አካላት በሚያደርገው ግብዣ መሠረት ከሚቀርቡት የፕሮጀክት ሀሳቦች መሀከል ይሆናል።

፫/ ኢንስቲትዩቱ የእያንዳንዱ የአርክቦት ውል ዘመን ሲያበቃ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከዚያም በፊት በማናቸውም ጊዜ ኢንስቲትዩቱ የፕሮጀክት ሀሳቦች የሚቀርቡበትንና የሚመረጡበትን መመዘኛዎች በመወሰን የፕሮጀክት ሀሳቦች እንዲቀርቡ አግባብነት ላላቸው የክልልና የፌዴራል አካላት ጥሪ ያደርጋል።

፬/ አሸናፊው ፕሮጀክት እንደተመረጠ፣ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ የሚሆን ገንዘብ ከአርክቦት ገንዘብ ሂሳቡ ወጪ ሆኖ ፕሮጀክቱን ለሚያስፈጽመው አካል ይከፈላል።

## ፳፰. የአርክቦት ገንዘብን ለማህበረሰቦች ጥቅም ስለማዋል

በአዋጁ አንቀጽ ፱ (፩) እና (፪) መሠረት ለማህበረሰቦች ጥቅም እንዲውል የተወሰነው የአርክቦት ገንዘብ የዚያ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት ባለቤት ለሆነው ማህበረሰብ ጠቀሜታ ለሚነደፉ የልማት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ይውላል።

2. The money to be obtained from each access agreement shall be deposited in a separate account in the access fund.

3. The Institute shall, upon the expiry of each access agreement, or, as necessary, at any time before such period, cause that the access money shall be put to use pursuant to the provisions of Articles 27 and 28 of this Regulation.

## 27. *Utilization of Access Money for Biodiversity Conservation*

1. The access money allocated for biodiversity conservation and promotion of community knowledge pursuant to Article 18(1) of the Proclamation shall be used to finance projects designed for the conservation and promote the sustainable utilization of the biodiversity resources and the associated community knowledge.

2. The biodiversity conservation projects shall be selected from project proposals submitted by the relevant regional and federal bodies upon invitation by the Institute.

3. Upon the expiry of each access agreement, or, as necessary, at any time before such period, the Institute shall invite the relevant regional and federal bodies to submit project proposals specifying the criterion for the submission and selection of project proposals.

4. Upon selection of the wining project, the project money shall be paid from the access money to the project implementer.

## 28. *Utilization of Access Money by Communities*

The access money allocated to the benefit of communities pursuant to Article 9(1) and (2) of the Proclamation shall be used to finance development projects designed to benefit the community which is the custodian of the genetic resources and/or the community knowledge accessed.

፳፱. ተጠቃሚውን ማህበረሰብ ስለመለየት

፩/ ኢንስቲትዩቱ ባካሄደው የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት ስርጭት ቅኝት ላይ በመመስረት አግባብነት ካላቸው የክልል አካላት ጋር በመመካከር ከእያንዳንዱ የአርክቦት ውል የሚገኘው ገንዘብ ተጠቃሚ መሆን የሚገባው ማህበረሰብ እንዲለይ ያደርጋል፡፡

፪/ የአርክቦት ገንዘቡ ተጠቃሚ የሆነው ማህበረሰብ የሚገኘው በተለያዩ ወረዳዎች፣ ዞኖች ወይም ክልሎች ውስጥ በሆነ ጊዜ፣ በነዚህ ወረዳዎች፣ ዞኖች እና ክልሎች ውስጥ የሚገኙት ማህበረሰቦች የተጠቃሚነት ድርሻ መጠን የጀነቲክ ሀብቱን እና/ ወይም የማህበረሰብ ዕውቀቱን ለመጠበቅ ካደረጉት አስተዋጽኦ አንፃር እየታየ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፴. የአርክቦት ገንዘብ አጠቃቀምን ስለመወሰን

ለማህበረሰቦች ጥቅም የሚዘረጉት የልማት ፕሮጀክቶች የሚወሰኑት፣ ተጠቃሚው ማህበረሰብ የሚገኘው፡-

፩/ በአንድ ወረዳ ውስጥ ብቻ ከሆነ፣ በወረዳው ምክር ቤት፣

፪/ በአንድ ክልል በተለያዩ ወረዳዎች ወይም ዞኖች ውስጥ ከሆነ፣ ከእነዚህ ወረዳዎች ወይም ዞኖች የተወከሉ የክልል ምክር ቤት አባላትን በማካተት በሚቋቋም የክልል ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴ፣ ወይም

፫/ በተለያዩ ክልሎች ውስጥ ከሆነ፣ ማህበረሰቡ ከሚገኝባቸው አካባቢዎች የተወከሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትን በማካተት በሚቋቋም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴ፡-

አማካይነት ይሆናል፡፡

፴፩. የፕሮጀክት ሀሳቦችን ስለማቅረብ

የእያንዳንዱ የአርክቦት ውል ዘመን ሲያበቃ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከዚያም በፊት በማናቸውም ጊዜ ኢንስቲትዩቱ፡-

፩/ ተጠቃሚው ማህበረሰብ የሚገኘው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ ከሆነ፣ ለማህበረሰቡ ጥቅም የሚውሉ የልማት ፕሮጀክት ሀሳቦችን በማዘጋጀት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለውሳኔ ያቀርባል፤

፪/ ተጠቃሚው ማህበረሰብ የሚገኘው በአንድ ክልል ውስጥ ከሆነ፣ ለማህበረሰቡ ጥቅም የሚውሉ የልማት ፕሮጀክት ሀሳቦች በማዘጋጀት የገንዘቡን አጠቃቀም ለሚወስነው የወረዳ ምክር ቤት ወይም የክልል ምክር ቤት ለውሳኔ እንዲያቀርብ የአርክቦት ገንዘቡን መጠን አግባብነት ላለው የክልል አካል ያሳውቃል፡፡

29. *Identification of Beneficiary Community*

1. The Institute shall, based on the survey it has undertaken on the distribution of genetic resources and/or community knowledge and in consultation with the relevant regional bodies, identify the community which shall benefit from the access money.

2. Where the beneficiary community resides in an area which lies in different Woredas, Zones or Regions, the relative share of the communities residing in such Weredas, Zones or Regions from the access money shall be determined based on their relative contribution to the conservation of the genetic resource and/or the community knowledge.

30. *Determining Utilization of Access Money*

The development projects deigned to benefit the communities shall be determined:

1. where the community resides only in one Woreda, by the Wereda Council;
2. where the community resides in different Woredas or Zones of one region, by the provisional committee of the regional council consisting of the members represented from such Woredas or Zones; or
3. where the community resides in an area which falls in different regions, by the provisional committee of the House of Peoples' Representatives consisting of members represented from the area where the community resides.

31. *Submission of Project Proposals*

Upon the expiry of each access agreement, or, as necessary, at any time before such period, the Institute shall:

1. where the beneficiary community resides in different regions, prepare project proposals designed to benefit the community and submit to the House of Peoples' Representatives for approval; or

2. where the beneficiary community resides in one region, communicate to the relevant regional body the amount of access money obtained so that it shall prepare project proposals designed to benefit the community and submit to the Wereda Council or the Regional Council which shall determine the utilization of such money.

፴፪. የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ- ሥርዓት

የወረዳ ምክር ቤቶች፣ የክልል ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴዎች እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጊዜያዊ ኮሚቴዎች የአርክቦት ገንዘብ ጥቅም ላይ የሚውልበትን የልማት ፕሮጀክት የሚወስኑት የምክር ቤቶቻቸውን የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት በመከተል ይሆናል።

፴፫. ወጪን ስለመሸፈን

ለማህበረሰብ ጥቅም የሚነደፉ የልማት ፕሮጀክቶችን ለማስወሰን ወጪ የሚጠይቅ ከሆነ ወጪው ከማህበረሰቡ የአርክቦት ገንዘብ ድርሻ ላይ የሚሸፈን ይሆናል።

ክፍል አምስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴፬. የአርክቦት መዝገብ

፩/ ኢንስቲትዩቱ ለሕዝብ ክፍት የሆነ የአርክቦት መዝገብ ይይዛል።

፪/ የአርክቦት መዝገቡ የሚከተሉትን ሰነዶች ያካትታል፦

ሀ) የአርክቦት ማመልከቻዎችን፣

ለ) የአርክቦት ማመልከቻዎች ውድቅ የተ ረገባቸውን ውሳኔዎች፣

ሐ) የአርክቦት ማመልከቻዎች ለሕዝብ የተገለፁባቸውን ማስታወቂያዎች፣

መ) በአርክቦት ማመልከቻዎች ላይ የቀረቡ መቃወሚያዎችንና አስተያየቶችን፣

ሠ) የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ውሎችን፣

ረ) የተፈረሙ የጀነቲክ ቁስ ማስተላለፊያ መደበኛ ስምምነቶችን፣

ሰ) የአርክቦት ፈቃዶችን፣

ሸ) የአርክቦት ውል ክትትልና ቁጥጥር ሪፖርቶችን፣

ቀ) የአርክቦት ውል ማሻሻያዎችን፣ ዕገዳዎችን ወይም መቋረጦችን፣

በ) የአርክቦት ውሎችን እና የጀነቲክ ቁስ ማስተላለፊያ መደበኛ ስምምነቶችን በሚመለከት የተሰጡ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን።

፴፭. የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ሃላፊነት

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ሀላፊነት ይኖሩታል፦

፩/ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልግ መመሪያ የማውጣት፣

፪/ አግባብነት ያላቸውን አካላት በማስተባበር ለክልሎች የቴክኒክ ድጋፍ የመስጠት፣

*32 Decision Making Procedure*

The Wereda Council, the provisional committees of Regional Councils and the provisional committees of the House of Peoples' Representatives shall determine the utilization of access money in accordance with the procedure of their respected councils.

33. *Cost*

Where cost is involved to get determined the development projects to benefit communities, it shall be covered from the community's share of the access money.

PART FIVE
MISCELLANEOUS PROVISIONS

34. *Access Register*

1. The Institute shall keep a register of access which shall be open to public.

2. The access register shall include:

(a) access application;

(b) dismissal of access application;

(c) public notice of access application;

(d) objections and opinions on access application;

(e) access agreements;

(f) standard material transfer agreements signed;

(g) access permit;

(h) access follow-up and monitoring reports;

(i) amendments, suspension and termination of access agreements; and

(j) court decisions related to access agreements, and standard material transfer agreements signed.

35. *Powers and Responsibility of the Institute*

The Institute shall have the following powers and responsibilities:

1/ to issue directives necessary for the implementation of this Regulation;

2/ by coordinating the relevant institutions, to provide the necessary technical support to regions;

፫/ በባለብዙ ወገን የአርክቦት ሥርዓቱ የሚሸፈን የጀነቲክ ሀብት በእጃቸው የሚገኝ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች የጀነቲክ ሀብቱን በባለብዙ ወገን ሥርዓቱ ውስጥ እንዲያካትቱ የማበረታታት።

፴፮. የክልሎች ሥልጣንና ሃላፊነት

ክልሎች የሚከተሉት ሥልጣንና ሀላፊነቶች ይኖራቸዋል:-

፩/ ይህንን ደንብ በክልላቸው ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ማውጣት፤ እና

፪/ ይህንን ደንብ በክልላቸው የሚያስፈፅም አካል የመሰየምና የማጠናከር።

፴፯. ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

ማናቸውም ደንቦች፣ መመሪያዎች ወይም አሠራሮች ይህንን ደንብ እስከተቃረኑ ድረስ በዚህ ደንብ ውስጥ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

፴፰. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፴ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

3/ to encourage any person in the country who is in possession of a genetic resource under the multilateral system of access to include the same into the multilateral system of access.

36. *Responsibility of Regions*

Each regional state shall have the following powers and responsibilities:

1/ enact detailed regulations necessary to implement this Regulation in their respective regions; and

2/ designate and strengthen institutions at all levels that shall implement this Regulation.

37. *Inapplicable Laws*

No regulations, directives or practices shall, in so far as they are inconsistent with this Regulation, be applicable with respect to matters provided for by this Regulation.

38. *Effective Date*

This Regulation, shall enter in to force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, on this 9th day of November, 2009

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አባሪ - ፩

ለንግድ ዓላማ የሆነ አርክቦት ማመልከቻ ፎርም

፩. ጠቅላላ መረጃ

፩.፩ የተፈጥሮ ሰው የሆነ የአርክቦት አመልካች የሚያቀርበው መረጃ:-

ሀ) የአመልካቹ ሥም፤

ለ) አድራሻው፤

ሐ) ያለው ሙያ (ካሪኩለም ቪቴ ይያያዛል)::

፩.፪ በሕግ የሰውነት መብት ያለው የአርክቦት አመልካች የሚያቀርበው መረጃ:-

ሀ) የድርጅቱ ስም፤

ለ) የተመዘገበ አድራሻው፤

ሐ) የተቋቋመበት ሰነድ (የሰነዱ ኮፒ ይያያዛል)፤

መ) በታቀደው ፕሮጀክት ውስጥ የሚሳተፉት ሰዎች የስም ዝርዝርና ሙያ (ካሪኩለም ቪቴ ይያያዛል)፤

ሠ) የድርጅቱ ዝርዝር ሁኔታ:-

i) እናት ወይም ቅርንጫፍ ኩባንያዎች፤

ii) ከአርክቦት ፕሮጀክቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ግለሰቦች ዝርዝር፤

iii) የአርክቦት ማመልከቻውን በሚመለከት ማናገር የሚቻለው ሰው ስም፣ አድራሻ እና በድርጅቱ ውስጥ ያለው ሀላፊነት::

፪. ዝርዝር የአርክቦት መረጃ

፪.፩ ገንዘብ ነክ መረጃ

ሀ) የአርክቦት ፕሮጀክቱ በጀት፤

ለ) የአርክቦት ፕሮጀክቱን በገንዘብ የደገፉ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ካሉ ዝርዝራቸው::

፪.፪ የቴክኒክ መረጃ

ሀ) ለማርከብ የተፈለገው የጀነቲክ ሀብት ዓይነት ዝርዝር:-

i) ስለጀነቲክ ሀብቱ ሳይንሳዊ መረጃ፤

ii) ጀነቲክ ሀብቱ ወይም የርሱ ውጤት የሚሰጠው ወይም ወደፊት ሊሰጥ የሚችለው ጠቀሜታ፤

iii) የጀነቲክ ሀብቱ ሊሰበሰብ የታሰበበት አካባቢ (የሚታወቅ ከሆነ)፤

iv) የጀነቲክ ሀብቱ ሊገኝ የሚችልባቸው ሌሎች አካባቢዎች ዝርዝር (የሚታወቅ ከሆነ)፤

ANNEX – I

FORM OF COMMERCIAL ACCESS APPLICATION

*1. General Information*

1.1 Information to be supplied by an access applicant who is natural person:

(a) name of applicant;

(b) address;

(c) qualifications (curriculum vitae to be attached).

1.2 Information to be supplied by an access applicant who is legal person:

(a) name of organization;

(b) registered address;

(c) establishment document (copy of the document to be attached);

(d) names and qualification of individuals participating in the proposed project (curriculum vitae to be attached);

(e) details of the organization:

(i) holding or subsidiary companies;

(ii) individuals connected with the project;

(iii) name and address of the contact person in regard to the application and the position held in the organization.

2. Detailed Access Information

2.1 Financial details:

(a) the budget for the project;

(b) details of institution or individual that sponsored the project, if any.

2.2 Technical Particulars:

(a) Details of the genetic resource to be accessed:

(i) scientific tax;

(ii) the actual and potential uses of the genetic resource and its derivatives;

(iii) the specific locality where the collection is intended to be undertaken, if known;

(iv) other possible locations of the genetic resource, if known;

v) ለማርከብ የተፈለገው ጀነቲክ ሀብት አካል መግለጫ (ሕብረ ሕዋስ፣ ዘር፣ ቅጠል ... ወዘተ)፤

vi) የሚሰበሰበው ጀነቲክ ሀብት መጠን፤

vii) ከጀነቲክ ሀብቱ ጋር ተያይዞ የሚገኝ የማሕበረሰብ ዕውቀት፤

viii) አርክቦት የሚፈፀምበት የጀነቲክ ሀብት የሚገኘው በኢዘቦታ ከሆነ የጀነቲክ ሀብቱን ይዞ የሚገኘው ተቋም ማንነት።

ለ) የአሰባሰብ ተልዕኮው ዕቅድ ዝርዝር፡-

i) ለማርከብ የተፈለገውን የጀነቲክ ሀብት የሚያቀርበው ሰው ማንነት፤

ii) የጀነቲክ ሀብቱ የሚገኘው በመሰብሰብ ከሆነ የሚሰበሰብበት ስልት፤

iii) በጀነቲክ ሀብት አሰባሰብ ላይ ኢትዮጵያ ውያን ባለሙያዎችና ተቋሞች የሚሳ ተፉ ከሆነ እነማን እንደሆኑ፤

iv) የጀነቲክ ሀብት አሰባሰቡ የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበት ጊዜ ሰሌዳ፤

v) አመልካቹ የጀነቲክ ሀብቱን ለመለየትና ለመሰብሰብ ድጋፍ የሚፈልግ ከሆነ የሚፈልገው የድጋፍ ዓይነት።

ሐ) ጀነቲክ ሀብቱ የሚውልበት አገልግሎት ዝርዝር፡-

i) ጀነቲክ ሀብቱ ሊውል የታሰበበት ጠቀሜታ፤

ii) የምርምሩ ዓይነትና ጥልቀት እንዲሁም ጥቅም ላይ የሚውለው የባለሙያና የመሣሪያ ዓይነት፤

iii) ከምርምሩ የሚጠበቀው ውጤትና ምርምሩ የሚፈጀው ጊዜ ግምት፤

iv) ምርምሩና የማልማት ሥራው የተለያዩ ክፍሎች የሚካሄዱባቸው ቦታዎች፤

v) ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች በምርምሩ ውስጥ የሚሳተፉ ከሆነ የሚሳተፉበት ሁኔታና የተሳትፏቸው ጥልቀት፤

vi) በምርምሩ ውስጥ ሊሳተፉ እና ሂደቱን ሊቆጣጠሩ የሚችሉ ኢትዮጵያውያን ተቋ ማት እነማን እንደሆኑ (ሊታወቅ የሚችል ከሆነ)፤

vii) የጀነቲክ ሀብቱ መጀመሪያ እና በቀጣይነት ሊወሰድ የሚችልባቸው ቦታዎች፤

(v) the parts of the genetic resource to be accessed (tissues, seeds, leaves ...etc.);

(vi) quantity to be collected;

(vii) any community knowledge associated with the genetic resource;

(viii) in case the genetic resource is held in *ex-situ*, details of the institution holding it.

(b) Details of planned collection mission:

(i) identification of the provider of the genetic resource for which access is sought;

(ii) the collection method to be used if the genetic resource is intended to collected;

(iii) the names and particulars of Ethiopian nationals and institutions, if any, intended to participate in the collection mission;

(iv) expected date of start and completion of the collection mission;

(v) give details, if applicant requires assistance to identify and collect the genetic resource.

(c) Details of the proposed use of the genetic resource:

(i) the type of use to which the genetic resource will be put;

(ii) the type and extent of the research as well as the expertise and equipment to be used;

(iii) the expected research result and the estimated time of completion;

(iv) the places where each element of the research and development program will take place;

(v) the manner and extent of participation of Ethiopian nationals in the research, if any;

(vi) national institutions which will participate in the research and be in charge of monitoring the process if known;

(vii) the primary and the probable subsequent destinations of the genetic resource;

viii) የአርክቦት አመልካቹ የውጭ ሀገር ዜጋ ከሆነ፣ ከሀገሩ መንግሥት ሥልጣን ያለው አካል አመልካቹ የአርክቦት ፈቃድ ቢሰጠው የሚኖርበትን የአርክቦት ግዴታዎች በዚያ ሀገር የሚያስከብርና የሚያስፈጽም መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ።

መ) የጥቅም ተጋሪነት መረጃ:-

i) የታቀደው የጥቅም መጋራት ስልትና የአተገባበር ሁኔታ ዝርዝር፤

ii) ለሀገሪቷ ወይም ለሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ ይገኛል ተብሎ የታሰበው ወይም ሊገኝ የሚችለው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ቴክኖሎጂያዊ፣ ሳይንሳዊ፣ አካባቢያዊ ወይም ሌሎች ማናቸውም ጥቅሞች ዝርዝር፤

iii) አርክቦት ማመልከቻው ላይ በበቂ ግንዛቤ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለመስጠት ሊረዳ ይችላል በማለት የአርክቦት አመልካቹ የሚገምተው ሌላ ማናቸውም መረጃ።

፫. የቃለ መሐላ ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት የአርክቦት አመልካች በዚህ ማመልከቻ ውስጥ የጠቀሰው መረጃ ትክክለኛና እውነት መሆኑን በመሐላ ቃል አረጋግጣለሁ።

፬. ፊርማ

የፈራሚው ስም ____________________

ሀላፊነት (በህግ የሰውነት መብት የተሰጠውን አካል በመወከል ሲሆን) ____________________

ፊርማ ____________________

ቀን ____________________

አባሪ - ፪

ለንግድ ላልሆነ ዓላማ አርክቦት ማመልከቻ ፎርም

፩. ጠቅላላ መረጃ

፩.፩ የአማልካቹ ተቋም ስም፤

፩.፪ የአመልካቹ ተቋም አድራሻ፤

፩.፫ የአመልካቹ ተቋም የተቋቋመበት ሰነድ (ተቋሙ የተቋቋመበት ህግ ወይም የምዝገባ ሰርተፊኬት እንዲሁም ተቋሙ በኢትዮጵያ የሚገኝ በይነ-መንግሥታዊ ተቋም ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሠራ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ያደረገው ስምምነት ኮፒ ይያያዛል)።

፪. ዝርዝር የቴክኒክ መረጃ

፪.፩ ስለጀነቲክ ሀብቱ ሳይንሳዊ መረጃ፤

(viii) where the access applicant is a foreigner, confirm that he can present a letter from competent authority of his national state or that of his domestic assuring that it shall uphold and enforce the access obligations if the applicant is granted access.

(d) Benefit sharing information:

(i) details of the proposed mechanisms and arrangements for benefit sharing;

(ii) the economic, social, technical, bio-technological, scientific, environmental or any other benefits that are intended, or may be likely, to accrue to the country or the concerned local communities;

(iii) any other information which the access applicant think might be useful to make an informed decision on the access application.

3. *Sworn Statement*

I, the undersigned access applicant, hereby confirm by a sworn statement that the information contained in this access application is correct and truthful.

4. *Signature*

Name of signatory ..............................................

Position (in the case of representing a a legal person) ..............................................

Signature ..............................................

Date ..............................................

ANNEX-II

FORM OF NON-COMMERCIAL ACCESS APPLICATION

1. General Information

1.1. Name of the applicant Institution;

1.2. Address of the applicant Intuition;

1.3. Establishment document of the institution (copies of the establishment legislation, or registration certificate, and, if the institution is an inter-governmental institution, the agreement concluded with Ethiopian Government to operate in Ethiopia).

2. Technical Information

2.1 specific taxa of the genetic resource;

፪.፪ ጀነቲክ ሀብቱ የሚገኝበት ቦታ፤

፪.፫ የጀነቲክ ሀብቱ ሊውል የታሰበበት ጠቀሜታ ዝርዝር፤

፪.፬ የታሰበው ምርምር ዓይነትና ጥልቀት እንዲሁም ጥቅም ላይ የሚውለው የባለሙያና የመሣሪያ ዓይነት፤

፪.፭ ምርምሩ የሚፈጅው ጊዜና ከምርምሩ የሚጠበቀው ውጤት

፪.፮ የምርምሩ የተለያዩ ክፍሎች የሚካሄዱባቸው ቦታዎች

፪.፯ የጀነቲክ ሀብቱ መጀመሪያ እና በቀጣይነት ሊወሰድ የሚችልባቸው ቦታዎች፤

፪.፰ ምርምሩ በጠቅላላ ወይም የምርምሩ ክፍል የሚካሄድበት ቦታ ከኢትዮጵያ ውጪ በሆነ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ መካሄድ የማይችልበት ምክንያት ዝርዝር።

፫. የመሀላ ቃል

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት የአርክቦት አመልካች በዚህ ማመልከቻ ውስጥ የጠቀስው መረጃ ትክክለኛና እውነት መሆኑን በመሐላ ቃል አረጋግጣለሁ።

፬ የአመልካቹ ፊርማ

የፈራሚው ስም ____________________

ሀላፊነት____________________

ፊርማ ____________________

ቀን ____________________

## አባሪ - ፫

## የባለብዙ ወገን አርክቦት ማመልከቻ ፎርም

፩. ጠቅላላ መረጃ

፩.፩ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ የአርክቦት አመልካች የሚያቀርበው መረጃ፤

ሀ) የአመልካቹ ስም ፤

ለ) የአመልካቹ አድራሻ ።

፩.፪ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው የአርክቦት አመልካች የሚያቀርበው መረጃ፤

ሀ) የድርጅቱ ስም፤

ለ) የድርጅቱ አድራሻ፤

ሐ) ድርጅቱ የተቋቋመበት ወይም የተመዘገበበት ሰነድ (የሰነዱ ኮፒ ይያያዛል)።

2.2 the specific locality of the genetic resource;

2.3 details of the proposed use of the genetic resource;

2.4 the type and extent of the research and the professionals and equipments to be used;

2.5 the estimated time of completion and the results expected of the research;

2.6 the places where each element of the research program will take place;

2.7 the primary and the probable subsequent destinations of the genetic resource;

2.8 if the research or part of it takes place outside of Ethiopia, the reason why it cannot be undertaken in Ethiopia.

3. Sworn Statement

I, the undersigned access applicant, hereby confirm by a sworn statement that the information contained in this access application is correct and truthful.

4. Signature

Name of the signatory ..............................................

Position ..............................................................

Signature: ...........................................................

Date: .................................................................

## ANNEX-III

## FORM OF ACCESS APPLICATION UNDER THE MULTILATERAL SYSTEM

1. General Information

1.1 Information to be supplied by an access applicant who is natural person:

(a) name;

(b) address.

1.2 Information to be supplied by and access applicant who is legal person:

(a) name of organization;

(b) registered address;

(c) establishment or registration document (copy of the document to be attached).

፪. <u>ለማርከብ የተፈለገው የጀነቲክ ሀብት ዝርዝር መግለጫ</u>

፪.፩ ስለጀነቲክ ሀብቱ ሳይንሳዊ መረጃ፤

፪.፪ ሊውል የታሰበበት አገልግሎት፤

፪.፫ ጀነቲክ ሀብቱን ይዞ የሚገኘው ወይም የሚያቀርበው ተቋም::

፫. <u>የመሃላ ቃል</u>

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት የአርክቦት አመልካች በዚህ ማመልከቻ ውስጥ የተጠቀሰው መረጃ ትክክለኛና እውነት መሆኑን እና በጀነቲክ ቁስ ማስተላለፊያ ስምምነቱ ውስጥ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችንና ግዴታዎችን የማከብር መሆኔን በመሓላ ቃል አረጋግጣለሁ::

፬. <u>ፊርማ</u>

የፈራሚው ስም ____________________

ሀላፊነት (በህግ የሰውነት መብት የተሰጠውን አካል በመወከል ሲሆን)____________________

ፊርማ ____________________

ቀን ____________________

2. Details of the genetic resource to be accessed

2.1 specific taxa;

2.2 intended purpose of use;

2.3 the institution holding, or the provider of, the genetic resource.

3. Sworn Statement

I, the undersigned access applicant, hereby confirm by a sworn statement that the information contained in this access application is correct and truthful and hereby confirm that I shall abide all the terms and conditions of the standard material transfer agreement.

4. Signature

Name of applicant ..............................................

Position (in the case of representing legal person) ..............................................

Signature ..............................................

Date ..............................................